# ይድረስ ለውድ ጠመኔ በቶሮቶ

ይድረስ ለውድ ጠመኔ በቶሮቶ፡፡ እንደምን ሰንብተሃል? እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ደህና ነኝ፡:

መቸም የእኔ ኩያና በጾታም ወንድ ነህ ብዬ በመገመት አንተ ብዬ ልጠራህ ነኝ። በኢትዮጵያ ፊርስት (Ethiopia First) ደህረ-ገጽ (web site) ላይ ያቀረብካቸው ጽሁፎች ጥሩ ናቸው። ይህቺን ጽሁፍም ያዘጋጀሁበት አንዱ ምክኒያት እንዳንተ ያሎትን በአማርኛ የሚጽፉትን ሙሁሮች ለመደገፍም ነው። አንተ እንዳልከው ሃሳብ መግለጽና ብሎም ሌላውን ማስተማር የሚቻለው ሰው በሚገባው ቋንቋ ጽሁፉ ሲቀርብ ነው። ዋናው ምክኒያት ግን አንተ ያመጣሃውን በሙሁር ላይ ያተኮረ ዲስኩር እያተነተንኩ ትችት ለመስጠት ነው።

ታዲያ ባንተው ጽሁፍ ላይ ለመተቸት ፈልጌ፡ ያገሩን ሰርዶ መሬት ባገሩ በሬ እንዲሉ፤ ያማርኛውን ጽሁፍ በእንግሊዝኛ አልተችም ብዬ፤ ያአማረኛ ሶፍትዌር (software) ከኮምፒውተሬ አስገብቸ ይህችን ጽሁፍ አዘጋጀሁ። ትንሽ ያማረኛው አጻጻፍ አስቸግሮኝ፡ ትእግስት አጥቸ ትቸው ነበር። የጣረ አንድ ነገር አያጣም እንዲሉ ለፍቸ ለፍቸ አጻጻፉን ተማርኩት። እንግዲህ ጠጅ በብርሌ፡ ነገር በምሳሌ እንዲሉ የራሴን ተመክሮ እያጣመርኩ ስለ ሙሁር ዲስኩር ልተች ነኝ።

አንተ ብቻ ሳትሆን ሌሎቹም በኢትዮጵያ ሙሁራን ላይ ብዙ ተችተዋል። በቅርቡ እንኳ በሪሁን አስፋው የሚባሉ በቶሮንቶ የሚኖሩ ሰው በኢትዮጵያውያን ሙሁራን ላይ በተመለከተ ጽፈዋል፤ ምንም እንኳ አጻጻፋቸው በግለሰብ ላይ ያተኮረ ቢሆንም።፡ ብርሃኑ ነጋም በቅርቡ በጻፉት መጽሃፋቸው ውስጥ የኢትዮጵያ ሙሁሮች የራስ ዝቅተኝነትና ጥቅም ፈላጊነት ጸባይ አላቸው ብለዋል። እርሻቸው ይህን ያሉበት ልዩ ምክኒያት ሊኖር ይችላል፤ የዚህ ጽሁፍ ጉዳይም አይደለም። ግን እንዲያው እንደኛ ያሉትን ቅን የድሃ ልጆች ጨምሮ በገፉ ሁሉም ሙሁር ጸባዩ አንድ ነው ማለታቸው ይሆን? እያልኩ አመናትቻሁ።

ባለፈው ሳምንት ካፒታል የተባለ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታታም ጋዜጣ ሶስት የአራተኛ አመት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሞባይል ስልክን አሰሰራር (operating system) ወደ አማርኛ ሊተረጉሙ እንደቻሉ አስታውቆናል። እነዚህ ልጆች ታታሪ ባላሙያዎች እንጂ ሙሁሮች አይደሉም። ስልክን ለመጀመሪያ የፈጠረው ካናዳዊው አሌክሳንደር ቤል ሙሁር አልነበሩም። ታዲያ ለምንድነው ኢትዮጵያውያኖች ሙሁር (ማለትም ማስትሬት ወይንም ዶክትሬት ያለው ሰው) አገር ያስተዳድራል፡ ኢኮኖሚውን ያለማል፡ ሳይንስና ጥበብን ያፈልቃል፡ ወዘተ፡ ብለው የሚያምኑት? መልሱን ለሌላ ጊዜ እንተወው። አንድ ሁላችንም የምንስማማበት ነገር ቢኖር ሁላቸውም እንደማንኛውም ሰው ጥቅማቸውን ያስቀድማሉ። እኔም ራሴ ትምህርቴን እንደጨረስኩ ኢትዮጵያ ሂጄ ድሃ ህዝብ አገግላለሁ እያልኩ ስፎክር ቆይቸ፤ ግን ትምህርቴን ስጨርስ ቦታዬን መድምጀ ቁጭ! የድሮው የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዬ

(supervisor) *ታዝቦኝ ሲሆን ሲሆን መጻፉን አታቋርጥ እያለ እያበረታታኝ ከርሱ ጋር እስከአሁን አብረን እንጽፋል።*

*ሙሁር ማለት ዲግሪ፡ ማስትሬት፡ ዶክትሬት፡ ወይም ሌላ የዘመናዊ ትምህርት ማእረግ ያለው ሰው ብቻ አይደለም። እንዲያውም እነሶቅራጥስ፡ አርስቶትል፤ ቅድስ አውገስቲን፡ ሩዙዎ፡ ማርክስ፤ አዳም ስሚዝ፡ ሌሎትቹም በታሪክ የታወቁት ፈላስፋዎች በኖሩብት ጊዜ ማስትሬት ወይንም ዶክትሬት የሚባል ነገር አይታወቅም። በዚህ ባለንበት ጊዜም በፍልስፍናም ሆነ በሳይንስ ዋና ዋና አስተዋጽኦ የሚያደርጉት ሰዎች ማስትሬት ወይንም ዶክትሬት ያላቸው አይደሉም። በሪሁን አስፋው ብዙ ምሳሌ ጠቅሰዋል። ሙሁር ማለት የሚያስብና የሚመራመር፡ የሚያስተውል፡ ቅንና የዋህ፡ ሰው አክብሮ እራሱን የሚያከብር፡ አርቆ የሚያስብ፡ የራሱን ትቶ የሌላውን ሰው ጥቅም የሚያስቀድም፡ ሰው የሚያስተምርና የሚያስታርቅ፡ ወዘተ፡ ግለሰብ ነው። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የት ይገሉ? የሚል ጥያቄ ከተነሳ፤ በየገዳማትና በየቤተክርስትያኖች የሚኖሩት ቀሳውስትና ሊቃውንቶች ምሳሌ ናቸው። በዘማናዊ ትምህርት ተምረው ላገራቸው ለማገልገል የተሰለፉ ሙሁሮች እንደነበሩም እናውቃልለን፤ አሁንም አሉ።*

*እንዲያው መቸም ጠመኔ ሌላ ነገር አመጣህብኝ ትለኛለህ እንጂ በሁለቱ አባቶቻችን በአቡነ ጳውሎስ እና አቡነ መርቆሬዎስ መካከል የተነሳው ጥል አሳስቦኛል። እንዲያው የኛ ነገር እልክ መጋባት እንጂ መቻቻል የለ። አቡነ ጳውሎስም እኛን በቅን የሚያገለግሉት ካህናት የጵጵስና ሹመት በአቡነ መርቆሬዎስ ሲሰጣቸው ከማውገዝ ይልቅ በመተሳሰብና በመግባባት መፍትሄ በተፈለገ ነበር። የቤተክርስቲያን ችግር አለነ ያልናቸው ይመስል ካህን እየሾሙ ወደኛ መላክስ ምን ይባላል? በርግጥ ብዙ ሰዎች ወደኛ ቤተክርስቲያኖች አይመጡም፤ ግማሾቹ በፖለቲካ ምክንያት ነው፤ ሌሎቹ ደግሞ እነከሌ ከሄዱበት አንሄድም እያሉ ነው። ታዲያ "ልጆቼ ተቻቻሉ ተግባቡ" ማለት ነው እንጂ ሌላ ካህን ወደዚህ መላክ ምን ጥቅም ያመጣል፤ የተሰደደውን ህዝብ ከመከፋፈል በስተቀር። ይልቁንስ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ገዳማት በችግር ምክኒያት እየፈረሱ ነው፤ መነኮሳትም እየተሰደዱ ነው ይባላል። ታዲያ የርሳቸው ትኩረት ወደዚህ ችግር ቢሆን ምናለ። አቡነ መርቆሬዎስም "አይ ልጆቼ፤ ይሄውላችሁ ተሰድጀ በመጣሁት አገር ደግሞ ፖለቲካ ተከትሎኝ መጣ" ብለው ዝም እንደማለት፡ አቡነ ጳውሎስን የሚያወግዝና የሚሺር መግለጫ አወጡ። ይህ ነገሩን አባባሰው። የቤተክርስቲያንዋን ህግ የሚያውቁ ሰዎችም ጣልቃ ገብተው ሁለቱን አባቶቻችን ያስማሙ። ደግሞ በፖለቲካ የኢትዮጵያ ድሃ ህብረተሰብ ይከፋፈል! እኒህ ነገር የሚያቀጣጥሉ ወረኛ ሰዎችም አቡነ ጳውሎስን መሳደቡን ያቁሙ። የነሱን ምሳሌ ተከትለው ሌሎቹ ደግሞ ነገ ካህናት ማንቋሸሽና መሳደብ ይጀምራሉ። ከድሮውም የመንግስት እጂ ባይኖርበት ይህ ሁሎ ጠንቅ አይፈጠርም ነበር።*

*ይቅርታና ወደኔው ነገር ልመለስ። ይህ ዶክተር፡ ፒ.ኤች.ዲ.፡ ፕሮፌሰር፡ ወዘተ፡ ብላችሁ ጥሩን የምንለው እኔንም አይገባኝም። በምእራባውያን አገሮች ሙሁሮች ዶክተር፡ ፒ.ኤች.ዲ.፡ ፕሮፌሰር፡ ወዘተ፡ እያሉ ራሳቸውን አይጠሩም። የትልቁ ልጄ*

ክርስትና አባት (ካናዳዊ) ፕሮፌሰር ናቸው። ከርሳቸው ቤተክርስቲያን ተጋብዤ በሄድኩ ጊዜ ፕሮፌሰር ወይንም ዶክተር ተብለው ሲጠሩ ሰምቼ አላውቅም። ካናዳ ውስጥ ከተማርኩባቸው ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እስከማውቀው ድረስ መምህራን (ፕሮፌሰሮች) ስማቸውን በቀላሉ (ለምሳሌ ጌ. መኳንንት) ብለው ጽፈው ከቢሮዋቸው ደጃፍ (በራፍ) ላይ ይለጥፋሉ። አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ አንድ ህንጻ ውስጥ ሶስተኛ ፎቅ ላይ ሄጄ የመምህራንን ቢሮ እየተዘዋወርኩ ስመለከት ከደጃፋቸው ላይ ዶክተር፡ ፒ.ኤች.ዲ፡ አቶ፡ ሚስተር (Mr.) (አንድ ፈረንጅ አለ) ብለው ጽፈው ለጥፈዋል። ከኛቹ ድህረ-ገጽ ላይም አንዳንዶቹ ዶክተር፡ ፒ.ኤች.ዲ፡ ቅብጥርሴ መሆናቸውን እያስታውቁ ጽሁፍ ያወጣሉ። በርግጥ ይህ ሁሉ የእያንዳንዱ ግለሰብ መብትና ምርጫ ነው። የኔ አስተሳሰብ ምንድን ነው፤ ልዩ መስለን ከመቅረብ ይልቅ እናቶቻችን፡ አባቶቻችን፡ መንድሞቻችንና እህቶቻችን መስለን ብንሰማራ ጥሩ ይሆናል የሚል ነው። ከነሱም እንማራለን፤ እኛም በደንብ ማስተማር እንችላለን። በድሮው ጊዜ ባላባቶች እንደኛ ያለውን የተራ ሰው ልጅ የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ ከሌለው እጃቸውን ዘርግተው ሰላም አይሎትም ነበር፤ ታዲያ ያኔ በትምህርት ደራጃ መመካት ተገቢ ነው ሊባል ይችላል። አሁን 21ኛው አ.ም. ደርሰናል። የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ተለውጧል። ገበሬ እንኳ ልጁን ለነጋዴ የሚያጋባበት ጊዜ ነው፤ በድሮው ጊዚማ እሺ አይልም።

በነገራችን ላይ እንደኔ ታዝበህ ከሆነ የኛቹ የውጭ አገር (Diaspora) ድህረ-ገጽ አዘጋጆች (web site hosts) በውጭ አገር ሙሁሮች የተጻፉትን ሃሳቦች እየጠቀሱ ለመጻፍና ለማውጣት (post) ውድድር ገጥመዋል፤ ተኮላ ሃጎስ እንኳ ሳይቀር። እንዲያው ከቶ አባ ገብረ ሃና ከሸክስፒር የማያንሱ መሆናቸውን ወይንም ዘራ ያቆብ ከአርስቶትል የማያንሱ መሆናቸውን ያውቁ ይሆን?

ቶሮንቶ ከሚገኘው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ አንድ ጥሩ ነገር ተምሬ ወጣሁ። አንድ ጊዜ፡ አንድ ጡሮታ የወጡ አስተማሪ የመስክ ጥናት ዘዴ (research methodology) ሊያስተምሩን መጡ። በክፍሉ ውስጥ እየዞሩ እያንዳንዱን ተማሪ "ምንድነው ለማጥናት ያሰብከው(ሽው)" እያሉ ጠየቁን። እኛም እያስረዘምነም እያሳጠርነም ትንሽም ውሸት እየጨመርነ የጥናት እቅዳችን ተናገርነ። የሁላችን ሃሳብና እቅድ ካዳመጡ በኋላ "ሁላችሁም ልክ አይደላችሁም" አሉ። "ጥናትና ምርምር የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እናንተ ጥያቄዎችን መዝግባችሁ ይዛችሁ መስክ ትወጣላችሁ፡፡ ለጥያቄዎቹ መልሶችን የሚሰጧችሁ ግን ሌሎቹ ሰዎች ናቸው። ምርምሩን የሚያደርጉትም እነሱ ናቸው። አብዛኛውም ከተመክሮ ያገኙት ነው። ሙሁሮቹ እነርሱ ናቸው። የእናንተ ጥናት ማለት የነሱን እውቀት መቅሰም፡ ገልብጦ መምጣትና መጻፍ ነው፡" ብለው አስረዱን።

በፈረንጆች አቆጣጠር 1997 አ.ም. ከአንድ ካናዳዊ ዲፕሎማት ጓደኛዬ ጋር ከአዲስ አባባ ወደ ጎንደር ሄድነ። ገጠር ማዬት እፈልጋለሁ ስለአለኝ ወደ ቤተሰቦቸ ልወስደውም ወሰንኩ። እንግዲህ ከዚያ በፊት አባቴ፤ በሰማይ ነብሱ ይማርና፤ ሳትነግረኝ እንግዳ ይዘህ ወደ ቤቴ እንዳትመጣ ብሎ አስጠንቅቆኛል። ይህ የሆነበትም ሞክኒያት አንድ ቀን ሁለት የግብርና ሚኒስቴር ሰራተኞችን ይዤ ሳያስብ ብቅ ብየበት ነው። ገጠር የምገናኛቸውን የመንግስት ሰራተኞች ሁሉ ወደ ቤቱ ስወስድ፤ ቀደም ብየ እስከተናገርኩ ድረስ፡ የ82ቱ አዛውንት አባቴ ቤቱን

አስተካክሎ ምግብ አሰርቶ፤ በደንብ አስተናግዶ ይሸኛቸዋል። ታዲያ የፈረንጂ እንግዳ ይገፔ ስሄድ የበለጠ መስተንግዶ ጠብቄ ነበር። ለኛማ ብርቅን አይደለም! አስቀድሜም መልእክት ልኬ እንዲዘጋጅ አስታውቄም ነበር። መኪናዋን ከመንገዱ ዳር አቆምንና 10 ደቂቃ ዳገቱን ወጥተን ያ የካናዳው ባለስልጣን፡ ሚስቱ እና ሁለቱ ልጆቹ ቤት ደረስነ። አምላክህ አለ ጠመኔ፤ እንኳን ቤት ሊሰናዳ ቀርቶ፤ እኛ ወደ ቤቱ ልንደርስ ስንቀርብ ከርሻው ሲሰራ እንደነበር፤ ስትጭር የዋለች ዶሮ መስሎ ብቅ አል። ከሱ ጋር ቢወዳደር የከተማው የጎንደሩ ለማኝ ጆሊ ነው። ይህ መናጢ ሽማግሌ አዋረደኝ ብዬ በጣም ተናደድኩኝ። ደግሞ ሳያፍር ቤት ግቡ እያላ ይገፋፋቸዋል። እኔ ጀግናው ግን ውርደት ይበቃል አልኩና፤ እንሂድ ጠጣና ጭላዳ እንይ ብዬ አታልዬ ወደ ተራራው ይዣቸው ወጣሁ። ትንሽ ቆይተውም ደከማቸውና ወደ ጎንደር እንመለስ አሉ። እነሱ ወደ መኪናው ተምልሰው ሲሄዱ እኔ ወደ አባቴ ቤት አመራሁ፤ ባይሆን ልስደበውና ንዴቱ ይውጣልኝ ብዬ። ከበራፉ ላይ ወንበር አድርጎ ተቀምጦ አገኘሁት። "እንዴት እንደዚህ ታዋርደኛለህ፤ ሲሆን ሲሆን ንጹህ ልብስ እንኳን አትለብስም?" ብዬ ጮክኩበት። "ምን ይላል አያ፤ ደሞ ለፈረንጅ ልጨነቅ" ብሎ ተነስቶ ጥሎኝ ሄደ። "ለነጫጭባ (ፈረንጅ) ጓደኛው ሳላሽረግድ ቀርቸ ተኮርፎኝ" እያለ በየአረቂ ቤቱ መተረቻ አደረገኝ። እድሜ ለኔ እንጂ በአካባቢው ያለእርሱ ገንዘብ ያለው ሰው የለ። ተከታዩው ብዙ ነበር። በዚህ ምክኒያት ስመጥር ሆንኩ።

ለመሆኑማ የምታስታውስ ከሆነ ከጥቂት አመታት በፊት አንድ የፋናንሻል ታይምስ (Financial Times) ጋዜጠኛ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር። እ.አ.አ. 1920 በፊት መሰለኝ፤ አንድ ከምስራቅ አፍሪካ ምናልባትም ከኬንያ ወይንም ታንዛንያ የመጣ ፈረንጅ አዲስ አባባ ሰነበተና ወደ ጂቡቲ ለመሄድ ፈለጎ ባቡር ጣቢያ ሄደ። እንግዲህ መርሳት የሌለብህ በዚያን ጊዜ ፈረንጆች አፍሪካውያንን ረግጠው እየገዙ እንደእንሰሳ ይቆጥሯቸውም ነበር። ታዲያ ያ ፈረንጅ ከምስራቅ አፍሪካ ለምዶ ደረቱን ነፍቶ ወደ አዲስ አባባ ባቡር ጣቢያ ሄደ። ዘበኛው ወይንም አስተናጋጁ ወደ ሶስተኛ ክፍል (third class) ግባ ይለዋል። ፈረንጁም ደንግጦና ተቆጥቶ ለምን? ብሎ ይጠይቃል። ዘበኛውም "አንደኛው ክፍል የሹማምንቶች ነው። ሁለተኛው ክፍል የመኳንንቶች ነው። ሶስተኛው ክፍል የተራ ህዝብ ነው፤ አንተም ጭምር" ብሎ ነገረዋ። ያ ፈረንጅም እየተከዘና እየተናደደ ጂቡቲ ገባ። ጋዚጠኛው ይህን የተረከው በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተነሳ ነው። እኒህ ጠቅላይ ሚኒስትር ኩራተኛና ትቢተኛ ናቸው! የእርዳታ ድርጅት ሰዎች ሊያነጋግሯቸው ሲመጡ እኔ አውቃለሁ እኔን ስሙኝ እንጂ የነሱን አያዳምጡ። ቢሆንም ግን ሰው የሚናገረው መስማት ጥሩ ነው። አሁን በእስር ቤት ውስጥ ያሉትን ሰዎች ይለቀቁ እያልን ብንማጸን ወይ ፍንክች! የናቀ ወደቀ እያሉ አባቶታችን ይተርታሉ።

እነዚህን ሁለት ምሳሌ ያቀረብኩበት ምክኒያት እኛ ታሪክ፡ ክብርና ኩራት ካለው ህብረተሰብ ውስጥ ተወልድን ያደግን ነን ለማለት ያህል ነው። ይህ አሁን የሚታዬው የሙሁር ድክመት አንዱ ምክኒያቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የዘመናዊ ትምህርት አጠቃቀም ከመጀመሪያኑ የተበላሸ ስለነበር ነው። በዘመኑ አገሪቱን ይገዟት የነበሩት ንጉሶች በዘመናዊ ትምህርት የሰለጠኑትን መንግስት ውስጥ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን አስያዟቸው። አገር ወዳዶች፤ ያልተማሩ ባላገሮችን፤ የቤተክርስትያን ሊቃውንቶችንም ጭምር፤ ከተማሩ ወጣቶች ስር ሆነው እንዲሰሩ

ተደረጉ አልያም ከስራ ተወገዱ። እነዚህ ጥቂት የተማሩ ሰዎች መንግስቱንና የመንግስቱን ንብረት ተቆጣጠሩት። ትንሽ ቆይተውም ባለጉ። አገሪቱን ሙልጭ አድርገው በልተው፣ አልያም ቤተሰቦቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ጠቅመው ስልጣን ለቀው ተበታተኑ። አንዳዶችም እዚህ ውጭ አገር መጥተው የ77 ሚሊዮን ህዝብ ተጠሪ ነን እያሉ ያወራሉ። ሞላጫዎች! እባካችሁን ጥሩ የተሰራውን እውቅና እንስጥ፣ ጥሩ ያልተሰራውን ቢሆን ማሻሻያ መንገድ ፈልገን ሃሳብ እናቅርብ ካልሆን ደግም በጥሩ መልክ እንቃወም፣ ተቃዋሚ ሃይሎችንም የተሳሳተ ፖለቲካ መስመር እንዲይዙ አንገፋፋቸው፣ ብለን ብንናገር የወያኔ አባሪ ብለው ጠሩን። ጉድ እኮነው!

አንድ ቀን ኢትዮጵያ ለመስክ ጥናት ሄጄ የሆንኩትን ደሞ ልንገርህ። ወሩ ጥቅምት ነበር። የጽጌ ወራት ነው። በዚህም ወቅት ህዝቡ ቤተክርስቲያን አካባቢ ተሰባስቦ ማህበር ይጠጣል። ታዲያ እስክሪቢቶና ደብተሬን ያዝኩና ወደ ቤተክርስቲያ ሄድኩ፣ እነኚህን ማህበራት ላጠና። በጠቅላላው አምስት ማሃበራት ነበሩ። ከያንዳንዱ ማህበር በገባሁ ጊዜ ጠላ ጠጣሁ፣ ገብሱን ቆሎም አነክትኩት። ግን "ብቅል አትዘናንቅ" የሚባለውን ያባቶቻችን አባባል ረስቸ። ብቅል (ጠላው) ከቆሎው ጋር ከሆዴ ውስጥ ፈላና በደም ስሬ አድርጎ ራሴ ላይ ወጣ። ከአራተኛው ማህበር ስደርስ ብን ብዬ ሰከርኩ። እንደተደለማደው አመስግኘ ለመውጣት ተነሳሁና "ስለ ትብብራችሁ አመሰግናለሁ፣ thank you very much" ብዬ ተሰናበትኩ። ከመጨረሻው ከአምስተኛው ማህበር ስደርስ ገና ብቅ ስል አንዱ ማህበርተኛ "እሄውልህ ከውጭ አገር የመጣው ሙሁር ገባ፣ እንግዲህ ጸጥ ብለህ ስማ" ሲል፣ እኔም ኩራቱም ስካሩም ተጨመረና ደረቴን ገልብጨ ወደ ማህበሩ ገባሁ። ልቀመጥ አሰብኩና ግን ሰውነቴ ዝሎ ስለነበር ምናልባት ተቀምጬ መልሼ መነሳት ቢያቅተኝስ አልኩና፣ እንደቆምኩኝ ሳልቀመጥ ንግግሩን ጀመርኩቷ! መጀመሪያ ሶስት ፍሬ (ቃል) አማርኛ አንድ ፍሬ እንግሊዝኛ እያደረኩ ተናከርኩ። ትንሽ ቆይቸ ሁለት ፍሬ አማርኛ እና ሁለት ፍሬ እንግሊዝኛ አደረኩት። ከዚያ በኋላ ንግግሩም ሰለጠኘ፣ እንግሊዝኛው ቀለለኘ። "Let me tell you more about my research" እያልኩ አንድ እጀን ከኪሴ ከትቸ ትንሽም እንደመወሳወስ እያልኩ አመጣሁታ! አንዱ አኳኋኔን የተገነዘበ ማህበርተኛ "አይ እንግዲህ በቃህ ቁጭ በል፣ ተንጃጃህ" አለና ጎቶ አስቀመጠኝ። እንዲች ነች ሙሁር ማለት! የመስክ ጥናቱማ ተረስቶ!

እኔስ ብቅሉ በዝቶብኝ ነው። ለምንድነው የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣኖች በእንግሊዝኛ የሚንተባተቡት? መሰልጠናቸውን ለማሳወቅ ነው ወይንስ ህዝቡ የሚናገሩትን ሰምቶ እንዳይረዳቸው ፈልገው? ባለፈው አመት ነው ወይንስ ከዚያ በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አቶ ብርሃኑ ደረሳን የአዲስ አባባ ከንቲባ አድርገው መሾማቸውን ለፓርላማው ሲያስታውቁ፣ የአቶ ብርሃኑን የስራ ህይወት ታሪክ ዝርዝር ሲያነቡ እንግሊዝኛ ጨመሩበት። ለምሳሌ አቶ ብርሃኑ አለም ባንክ ነው ወይንስ አንድ የሆነ አለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ኮርፖሬት ሴክሬታሪ (corporate secretary) ሆነው ይሰሩ ነበሩ ብለው ተናገሩ። እግዚአብሄር ያሳይህ የርሳቸው ንግግር በዜና ማሰራጫዎች በመላው አገር ይተላለፋል። የኢትዮጵያ ህዝብ እንግሊዝኛ አያውቅም። ለነገሩማ የ200 ሺህ አመት መከበሪያ በአል እንደማለት "የምሊኒየም በአል" ብለው ሰየሙት አይደለም! እውነት እንናገር ከተባለ አማርኛ አነጋገር በመንግስቱ ሃይለ ማርያም ጊዜ ቀረ። አደባባይ ላይ ወጥተው

የውጭ አገር ቋንቋ ደብልቀው ተናግረው አያውቁም። ምናለበት ሰው ጥሩ በሰራው ቢመሰገን።

አንዴ አክሱም አድሬ ሽሬ ስደርስ የጎንደሩ አውቶቡስ አመለጠኝ። ሽሬ በምእራብ ትግራይ የምትገኝ ከተማ ናት። አውቶቡሱ ተራ ቆሜ የቀትር ጸሃይ ሲወቃኝ፤ አንድ ጎንደሬ ተዋወቅኩና ጠላ ቤት ይዞኝ ሄደ። ሁለቱን ሚኒሊክ (የቆርቆሮ ዋንጫ) ጠላ ክው አደረኩት። አይ የጠጣሁት ጠላ! እኔ ጀግናው ደግም ያደኩበትን ጠላ ከቀመስኩ እንኳን የቀትር ጸሃይ የኢጋም እሾህ አልፈራም። አውቶቡሱ ተራ ተመልሼ ተዝናንቸ ተቀምጩ እያለሁ እድሜያቸው ወደ 30 አመት የሚሆኑ ሁለት የከተማ ሰዎች መጡና አንዱን ከተከዜ በረሃ የመጣውን የታጠቀ ሰውዬ መሳደብ ጀመሩ። “የታባትክና ይህን መበንጃህን ቀምቸ ነው የምወስደው” እያለ አንዱ ይናገራል። ያ ቆለኛም አንገቱን ደፍቶ ራሱን ነቀነቀ። ጠጣ ከዛፍ ላይ ሆና ከአምበሳ ጋር ጠብ ትጭራለች ተብሎ ይተረት የለ፤ መቸም አንበሳ ዛፍ ላይ አይወጣም ብላ። ከከተማዋ ውጭ ቢሆንማ ያ ሰው በያዘው ጠመንጃ አንድ ነገር አድርጎ ተከዜ በረሃ ቢጋባ ነበር። እኔም ከወያኔ አገር ለካስ እንዲህ አይነት ነገርም አለ ብየ ተገረምኩ። ለመሆኑማ ትግራይ ውስጥ ስንጓዝ ሁለት ነው ሶስት ትንንሽ ከተማዎች የድሮውን የደርግን ወይንም የሃይለ ስላሴን ሰንደቃላማ ሰቅለው ሲያውለበልቡት አዬን አይደለም። ታዲያ እንዲህ ያለውን ለባህሉንና ታሪኩን አጥባቂ ህዝብ ከገገርው መደብ ፖለቲካ ጋር አያይዘን የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ ሀብት ተጠቃሚ ሆኗል እያልነ እንተርካለን። እግዚአብሄር ይቅር ይበለን። ባንጻሩማ የኛቹ ሙሁሮች ኢህአዴግ ስልጣን እንደያዘ አዲሱን (የኢህአዴግን) ሰንደቃላማ እያውለበለቡ ለስልጣን ሲሽቀዳደሙ አልነበሩንም? አንዳርጋቸው ጽጌ በአማራ ዘር ላይ ጻፉ። ለሎቹም የኢህአደግን ፓርቲና አስተዳደር እንደግፋለን ብለው ተሾሙ። በኋላ በተለያዩ ምክኒያቶች ከስልጣን ሲወርዱ ወይንም የሆነ ነገር ሲያጋጥማቸው “የፓለቲካ ልዩነት አለን” እያሉ ወደ ውጭ አገር ተጓዙ። የውጭ አገር ፖለቲካ ደርጅቶች የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ሆኑ። እስኪ እንዲያው ለምሳሌው የትግሬ ህዝብ ተጠቅሟል እንበል። ታዲያ እውነተኛ በኢትዮጵያ አንድነት የምናምን ሰዎች ባለፉት ብዙ ዘመናት ኢትዮጵያን ለመውረር በመጡ ጠላቶች ሁሉ ሲጎዳ የኖረ ህዝብ እስኪ አሁንስ ይረፍ፡ ትንሽ ይጠቀም ማለት የለብንም? መስፍን ወልደ ማርያም በዚህ የተነሳን ነው እስር ቤት ሆነው የትግራይን ህዝብ አትንኩ ብለው ተቆጥተው የጻፉት።

አይ ጠመኔ፤ የኛ ትውልድ ስንት ነገር አይቷል፤ ስንት ነገር ደርሶበታል። ብቻ ሆድ ይቻለው ብሎ ማለፉ ይሻላል።

*ውድ ወንድምህ ጌታቸው መኳንንት*
*ኦታዋ ካናዳ*
*መጋቢት 3 1999*